3ኛ ዓመት ቁጥር 24
3rd Year No. 24

ባህር ዳር መስከረም 30 1990 ዓ.ም
Bahir Dar 10th Oct.1997

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKER HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATINAL REGIONAL STATE IN THE FEDURAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.BOX

ማውጫ አዋጅ ቁጥር 24/1990 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1990 ዓ.ም ሥራዎች የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ገጽ 2	CONTENTS Proclamantion No-24/1997 A Proclamantion To provide Additional Budget For The Activities of The 1997/98 Of The Amhara National Regional State Page 2

አዋጅ ቁጥር 24/1990 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1990 ዓ.ም ሥራዎች የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ

ካለፉት አመታት ተርፎ ወደ 1990 በጀት ዓመት የተላለፈውን የመንግስት ገንዘብ የተጨማሪ በጀትና ለ1990 በጀት ዓመት ለመጠቀም አንዲቻል፤

የ1990 በጀት ዓመት ከተጀመረ ቡኋላ ለሚከናወኑ ተጨማሪ ሥራዎችና አገልግሎት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ በጀት አጽድቆ በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑን፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ሕገ-መንግስት መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት ማፅደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 በክልሉ ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት የክልሉ ተጨማሪ በጀት እንደሚከተለው ታውጇል።

Proclamantion No-24/1997
A Proclamation To provide Additional Budget For The Activities of The 1997/98 Of The Amhara National Regional State

Where as it is necessary to use the unutilized funds of the government, transferred to the budget year of 1997 from the previous, as an additional budget for the same year;

Where as it has become necessary to approve and implement the extra budget necessary for additional activity out of the commencement of the 1997 budget year;

Where as in accordance with the constiruion of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the power to approve and impliment its own budget is vested in the region;

Now, there fore,in accordance with the article 49 of the constitution of the Amhara national Regional State and article 21 of the proclamation of finance and adminstration of the region, the additional budget of the region is proclaimed as follows.

ክፍል 1
ጠቅላላ

አንቀጽ 1

ይህ አዋጅ "አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1990 ዓ.ም ሥራዎች የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 24/1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ለ1990 በጀት ዓመት የክልሉ ም/ቤት ካፀደቀው ብር 951,602,500 በተጨማሪ ካለፋት ዓመታት እስከ 1990 በጀት ዓመት በሥራ ላይ ካልዋለው፣ ብር 40,000,000 መደብ ባልተሠጣቸው ገቢዎች ስም ተይዞ የደመወዝ በጀት እጥረት ለተከሰተባቸው ዘኖችና ለሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችና አገልግሎቶች ክፍያ መክፍል እንዲቻል ተፈቅዷል።

አንቀጽ 3

ተጨማሪ በጀቱ በመጠየቂያ በጀት ስም ተይዞ በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መሠረት ለክልሉ መንግስት የተለያዩ ወጭዎች እንዲከፈል ተፈቅዷል።

ክፍል 2
የበጀት አስተዳደር

አንቀጽ 4

ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየመስሪያ ቤታቸው ሥራና አገልግሎት የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚቅድላቸውን በጀት የሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብ ቢሮ ሀላፊው ከተጠቀሰው ገቢ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል።

አንቀጽ 5

የክልሉ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የበጀት ዝውውር ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ 6

ይህ አዋጅ በክልሉ ም/ቤት ፀድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
መስከረም 30 ቀን 1990 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

PART 1
GNERAL

Article 1

This proclamation may be cited as " a proclamation to provide additional budget for the activities of the 1997/98 of the Amhara National Regional State No 24/1997"

Article 2

In addition to Birr 951,602,500 approved for the 1997 budget year by the council of the region, Birr 40,000,000 Unutilized since the previous years up to the 1997 budget year, is here by permitted being retained under "other revenue" to be paid for one with shortege of salary budget and payments for other additional activities and services.

Article 3

In accordance with the decision of the excutive committee of the regional state, it is here by permitted to pay the additional budget, being retained budget, for various expenditures of the regional state.

PART 2
Budget Adminstration

Article 4

The head of the Finance Bureau, is here by allowed and permitted to pay from the mentionead revenue to be permitted by the executive committee of the regional state, when the heads of the concerned bodies of the regional state demand payment for the activities and service of their respective office.

Article 5

Transfer of the budget shall be effected in accordance with the proclamation of finance administration of the regional state.

Article 6

This proclamation shall come in to force on the date of its ratificaion by the council of the Region

Done at Bahir Dar
This 10th day of oct. 1997
Council of the Amhara National Regional State